# የማዘጋጃ ቤት ምርጫ የመራጭ መመሪያ

**2025**

**የምርጫ ቀን እ.ኤ.አ ኖቬምበር 4 ቀን 2025 ዓ.ም ነው**

CITY OF CAMBRIDGE | Election Commission

## የመራጭ ምዝገባ፦

የመራጭነት ምዝገባ ሁኔታዎን **www.RegisterToVoteMA.com** ላይ ይመልከቱ ወይም በ**617-349-4361** ይደውሉ።

በመራጭነት ለመመዝገብ የተቀመጠው ቀነ ገደብ **እ.ኤ.አ ቅዳሜ፣ ኦክቶበር 25 ቀን 2025 ዓ.ም** ነው! **ወደ 689 Massachusetts Avenue የተዛዋወረው Election Commission Office ከ9 ኤ.ኤም እስከ 5 ፒ.ኤም ድረስ** ክፍት ይሆናል።

### ኦንላይን

የMassachusetts የመንጃ ፍቃድ ወይም መታወቂያ ካለዎት **www.registertovotema.com** ላይ ይመዝገቡ። ከሌለዎት ድር-ጣቢያውን መጠቀም የሚችሉ ቢሆንም፣ ቅጽዎን ግን ማተም፣ መፈረም እና ለElection Commission Office (የምርጫ ኮሚሽን ጽሕፈት ቤት) በፖስታ መላክ ይኖርብዎታል።

### በፖስታ

ከCity Clerk's Office (የከተማ አስተዳደር ጸሐፊ ጽሕፈት ቤት)፣ ከማንኛውም የCambridge ፖስታ ቤት ወይም ከማንኛውም የCambridge Public Library (የCambridge የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት) ቅርንጫፍ በፖስታ የሚላክ የምዝገባ ቅጽ ማግኘት ይችላሉ። ያጠናቀቋቸውን የምዝገባ ቅጾች በሚከተለው አድራሻ ይላኩ፦ **Cambridge Election Commission፣ 689 Massachusetts Ave፣ STE 1 Cambridge፣ MA 02139-3302።**

### በአካል

በአካል መመዝገብ ከፈለጉ **689 Massachusetts Ave** ላይ በሚገኘው Election Commission Office ሄደው መመዝገብ ይችላሉ። በRegistry of Motor Vehicles (የሞተር ተሽከርካሪዎች መዝገብ ቤት) የሚከናወነው እያንዳንዱ ሥራ አካል ተደርጎ እና በአንዳንድ የመንግሥት እርዳታ ኤጀንሲዎች የመራጭ ምዝገባን ማግኘት ይቻላል።


**ብቁነት፦** በCambridge ከተማ አስተዳደር ውስጥ በመራጭነት ለመመዝገብ የሚከተሉትን ማሟላት አለብዎት፦

- የUnited States ዜጋ መሆን
- የCambridge ከተማ ነዋሪ መሆን
- በዕድሜዎ 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ መሆን (በዕድሜያቸው 16 ወይም 17 ዓመት የሆኑ የCambridge ነዋሪዎች ቅድመ-ምዝገባ ማድረግ ይችላሉ።)

**ቀድሞውኑ በመራጭነት ተመዝግበዋል?**

በድጋሚ መመዝገብ የሚኖርብዎት **ስምዎን፣ መኖሪያ አድራሻዎን፣**የፖስታ አድራሻዎን ወይምየፖለቲካ ፓርቲዎን ከቀየሩ ብቻ ነው።

## ድምጽ መስጫ መንገዶች!




### በፖስታ ድምጽ ይስጡ

ለዚህ ምርጫ ሁሉም የCambridge መራጮች በፖስታ በኩል ድምጽ መስጠት ይችላሉ። ለተጨማሪ ዝርዝሮች ገጽ 3ን ይመልከቱ።

### ቀደም ብለው በአካል ድምጽ ይስጡ

በተመደቡ ሰዓታት ወቅት ከእነዚህ ሶስት ቦታዎች መካከል የትኛውም ላይ **እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 25** ጀምሮ እስከ **ኦክቶበር 31** ድረስ በሶስት ቦታዎች ላይ ቀደም ብሎ ድምጽ መስጠት ይቻላል (ገጽ 2ን ይመልከቱ)።

### በምርጫ ቀን ድምጽ ይስጡ

**እ.ኤ.አ ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 4 ላይ ከ7 ኤ.ኤም ጀምሮ እስከ 8 ፒ.ኤም** ድረስ የምርጫ ጣቢያዎች ክፍት ይሆናሉ። መራጮች በተመደበላቸው የምርጫ ጣቢያ ሄደው ድምጽ መስጠት አለባቸው (ገጽ 4ን ይመልከቱ)።

# ቀደም ብሎ በአካል ድምጽ መስጠት

## ቀደም ብሎ በአካል ድምጽ መስጠት የሚቻልባቸው ጊዜያት እና ቦታዎች

| | |
|---|---|
| **እ.ኤ.አ ቅዳሜ፣ ኦክቶበር 25 ቀን** | ከ9 ኤ.ኤም - 3 ፒ.ኤም |
| **እ.ኤ.አ እሑድ፣ ኦክቶበር 26 ቀን** | ከ9 ኤ.ኤም - 3 ፒ.ኤም |
| **እ.ኤ.አ ሰኞ፣ ኦክቶበር 27 ቀን** | ከ8:30 ኤ.ኤም - 8 ፒ.ኤም |
| **እ.ኤ.አ ማክሰኞ፣ ኦክቶበር 28 ቀን** | ከ8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም |
| **እ.ኤ.አ ረቡዕ፣ ኦክቶበር 29 ቀን** | ከ8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም |
| **እ.ኤ.አ ሐሙስ፣ ኦክቶበር 30 ቀን** | ከ8:30 ኤ.ኤም - 5 ፒ.ኤም |
| **እ.ኤ.አ አርብ፣ ኦክቶበር 31 ቀን** | ከ8:30 ኤ.ኤም - 12 ፒ.ኤም |

ማንኛውም የተመዘገበ መራጭ ቀደም ብሎ ድምጽ መስጠት ይችላል። ከምርጫ ቀን በተለየ መልኩ ቀደም ብሎ ድምጽ መስጫ ጊዜ ላይ የምርጫ ጣቢያ አይመደብልዎትም።

ከታች በተጠቀሱት ጊዜያት ላይ ከሶስቱ የCambridge ቀደም ብሎ ድምጽ መስጫ ቦታዎች መካከል ወደ የትኛውም መሄድ ይችላሉ።

**Valente ቤተ መጻሕፍት**
826 Cambridge Street፣ Berkshire Street ላይ ባለው የጎን መግቢያ

**Cambridge Water Department (የCambridge የውኃ መምሪያ)**
250 Fresh Pond Parkway

**Main library (ዋና ቤተ መጻሕፍት)**
449 Broadway

**689 Massachusetts Avenue ላይ የሚገኘው Election Commission Office ለማዘጋጃ ቤት ምርጫው እንደ ቀደም ብሎ ድምጽ መስጫ ጣቢያ አያገለግልም።**

# በምርጫ ቀን

### በምትኩ በምርጫ ቀን ድምጽ መስጠት ብፈልግስ?


ድምጽ መስጠት የሚችሉት አንድ ጊዜ ብቻ ነው—በፖስታ ወይም በአካል ቀርበው ቀደም ብሎ ድምጽ መስጫ ወረቀት በመጠቀም ድምጽ ከሰጡ የምርጫ ቀን ላይ ድምጽ መስጠት አይችሉም።

ቀደም ብለው ድምጽ ካልሰጡ፣ የምርጫ ቀን ላይ በተመደበልዎት የምርጫ ጣቢያ ድምጽ መስጠት ይችላሉ። እ.ኤ.አ **ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 4 ላይ ከ7 ኤ.ኤም ጀምሮ እስከ 8 ፒ.ኤም** ድረስ የምርጫ ጣቢያዎች ክፍት ይሆናሉ።

ከምርጫ ቀን በፊት የተመደቡበትን የምርጫ ጣቢያ የያዘ የመራጭ ማሳወቂያ ካርድ ይደርስዎታል። ድምጽ ለመስጠት በተመዘገቡበት ጣቢያ ድምጽ መስጠት አለብዎት። የእርስዎን የምርጫ ጣቢያ በሚከተለው ይፈልጉ፦


**www.sec.state.ma.us/VoterRegistrationSearch** ወይም በ**617-349-4361** ወደ Election Commission Office ይደውሉ።

የምርጫ ጣቢያዎች ዝርዝር ገጽ 4 ላይ ቀርቧል።






# በፖስታ ቀደም ብሎ ድምጽ መስጠት




## 01 እንዴት ማመልከቻ ማግኘት እንደሚቻል፦

ከ**www.cambridgema.gov/earlyvoting** ማመልከቻውን ያውርዱ ወይም የእርስዎን ስም፣ የCambridge አድራሻ፣ ድምጽ መስጫ ወረቀቱ እንዲላክ የሚፈልጉበትን አድራሻ እና ፊርማዎን የያዘ የጽሑፍ ጥያቄ በመላክ ድምጽ መስጫ ወረቀት ይጠይቁ።

## 02 ማመልከቻዎን መላክ የሚችሉባቸው አማራጮች፦

የተፈረመበት ማመልከቻዎን በኢሜይል፣ ፋክስ ወይም ፖስታ ይላኩ።

**elections@cambridgema.gov**

**Cambridge Election Commission፣689 Massachusetts Ave STE 1፣ Cambridge፣ MA 02139-3302**

**ፋክስ 617-349-4366**

## 03 ድምጽ መስጫ ወረቀትዎን መመለስ የሚችሉባቸው አማራጮች፦

1. ከድምጽ መስጫ ወረቀትዎ ጋር የቀረበውን ለፖስታ-የተከፈለበት ማሸጊያ በመጠቀም ድምጽ መስጫ ወረቀቱን በፖስታ ይመልሱ።
2. ድምጽ መስጫ ወረቀቶቹን **689 Massachusetts Ave** በሚገኘው Election Commission Office በአካል ቀርበው ይመልሱ።
3. ድምጽ መስጫ ወረቀቶቹን በተሰየሙ ቀደም ብሎ ድምጽ መስጫ ሰዓታት ላይ በተመደበ ቀደም ብሎ ድምጽ መስጫ ጣቢያ ለሚገኝ የምርጫ ኃላፊ በታሸገ ፖስታ ይመልሱ።
4. ድምጽ መስጫ ወረቀቶችዎን Cambridge ውስጥ ከሚገኙት ስድስት (6) ድምጽ መስጫ ሳጥኖች መካከል ወደ የትኛውም ያድርሱ። የድምጽ መስጫ ሳጥን መገኛዎች በዚህ መመሪያ የመጨረሻ ገጽ ላይ ተዘርዝረዋል።

### ወሳኝ ቀነ ገደቦች

እ.ኤ.አ **ከኦክቶበር ወር ሁለተኛው ሳምንት** ጀምሮ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች በፖስታ ይላካሉ።

ድምጽ መስጫ ወረቀቶችዎ በተገቢው ጊዜ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ እ.ኤ.አ **ማክሰኞ፣ ኦክቶበር 14** ሳያልፍ ማመልከቻዎን እንዲያስገቡ የElection Commission ይመክራል። ማመልከቻዎ እ.ኤ.አ **ከማክሰኞ፣ ኦክቶበር 28 ቀን 5 ፒ.ኤም** በኋላ ለElection Commission ከደረሰ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች በፖስታ ሊላኩልዎት አይችሉም።

ድምጽ መስጫ ወረቀቶች እንዲቆጠሩ እ.ኤ.አ **ከማክሰኞ፣ ኦክቶበር 4 ቀን 8 ፒ.ኤም** በፊት ለElection Commission Office መድረስ አለባቸው።

እ.ኤ.አ እስከ **ኦገስት 12** ድረስ ለተመዘገቡ የCambridge መራጮች የፖስት ካርድ ማመልከቻዎች በፖስታ እየተላኩ ነው። ፖስት ካርድ ባይደርስዎትም በፖስታ ድምጽ ለመስጠት ማመልከት ይችላሉ። ድምጽ መስጫ ወረቀቶች በፖስታ የሚላኩት በጽሑፍ ማመልከቻ ላቀረቡ መራጮች ብቻ ነው።

# ለምርጫ ቀን የሚያገለግሉ የምርጫ ጣቢያዎች

**222 Jacobs Street**፣ የስብሰባ ማዕከል .................................... 1-1

**M.I.T. Kresge አዳራሽ**፣ 70 Massachusetts Avenue፣ Stratton ማዕከል በስተጀርባ ........................ 1-2

**M.I.T. Kresge አዳራሽ**፣ 70 Massachusetts Avenue፣ Stratton ማዕከል በስተጀርባ ...................... 1-2A

**Millers River አፓርታማዎች**፣ 15 Lambert Street፣ Cambridge Street መግቢያ .............. 1-3

**Valente ቅርንጫፍ ቤተ-መጻሕፍት**፣ 826 Cambridge Street፣ Berkshire Street ላይ የሚገኘው የጎን መግቢያ 2-1

**Truman አፓርታማዎች**፣ 25 Eighth Street፣ Community Room፣ Thorndike Street መግቢያ ........................ 2-2

**O'Connell ቅርንጫፍ ቤተ-መጻሕፍት**፣ 48 Sixth Street፣ የThorndike Street ጫፍ ላይ፣ የኋላ መግቢያ ........ 2-3

**O'Connell ቅርንጫፍ ቤተ-መጻሕፍት**፣ 48 Sixth Street፣ የThorndike Street ጫፍ ላይ፣ የኋላ መግቢያ ...... 2-3A

**Pisani ማዕከል**፣ 131 Washington Street፣ ........................ 3-1

**Moses የወጣት ማዕከል**፣ 243 Harvard Street፣ የታችኛው ወለል፣ የኋላ መግቢያ .................. 3-2

**City Hall**፣ 795 Massachusetts Avenue፣ የመኪና መንገድ መግቢያ ........................ 3-3

**City Hall**፣ 795 Massachusetts Avenue፣ የመኪና መንገድ መግቢያ ...................... 3-3A

**Morse ትምህርት ቤት**፣ 40 Granite Street፣ ዋና መግቢያ ........ 4-1

**የSaint Peter ኤጲስ ቆጶስ ቤተ-ክርስቲያን**፣ ............................ 4-2
838 Massachusetts Ave፣ Sellers Street ላይ የሚገኘው መግቢያ

**የSaint Peter ኤጲስ ቆጶስ ቤተ-ክርስቲያን**፣ .......................... 4-2A
838 Massachusetts Ave፣ Sellers Street ላይ የሚገኘው መግቢያ

**Martin Luther King, JR. ትምህርት ቤት**፣ 102 Putnam Avenue፣ የመጫወቻ ሜዳ ጂም መግቢያ .... 4-3

**የSalvation Army ዋና መሥሪያ ቤት**፣ .................................. 5-1
402 Massachusetts Avenue

**M.I.T Kresge አዳራሽ**፣ 70 Massachusetts Avenue፣ ከStratton Center በስተጀርባ ........................ 5-2

**Morse ትምህርት ቤት**፣ 40 Granite Street፣ ዋና መግቢያ ........ 5-3

**የCity Hall አባሪ ህንፃ**፣ 344 Broadway፣ ሁለተኛ ፎቅ፣ የስብሰባ ክፍል ............ 6-1

**የCity Hall አባሪ ህንፃ**፣ 344 Broadway፣ ሁለተኛ ፎቅ፣ የስብሰባ ክፍል .......... 6-1A

**Cambridge Rindge & Latin ትምህርት ቤት**፣ 459 Broadway፣ Media ካፍቴሪያ፣ Cambridge Street መግቢያ ... 6-2

**Cambridge Rindge & Latin ትምህርት ቤት**፣ 459 Broadway፣ Media ካፍቴሪያ፣ Cambridge Street መግቢያ ... 6-3

**Baldwin ትምህርት ቤት**፣ Community Floor፣ 85 Oxford Street፣ Sacramento Street መግቢያ ... 7-1

**Baldwin ትምህርት ቤት**፣ Community Floor፣ 85 Oxford Street፣ Sacramento Street መግቢያ ... 7-2

**Baldwin ትምህርት ቤት**፣ Community Floor፣ 85 Oxford Street፣ Sacramento Street መግቢያ . 7-2A

**Gund Hall**፣ 48 Quincy Street፣ Cambridge Street መግቢያ ..... 7-3

**Graham and Parks ትምህርት ቤት**፣ 44 Linnaean Street፣ የመጫወቻ ሜዳ መግቢያ ............ 8-1

**Friends Center**፣ 5 Longfellow Park፣ Community Room ..... 8-2

**Martin Luther King, JR. ትምህርት ቤት**፣ 102 Putnam Avenue፣ የመጫወቻ ሜዳ ጂም መግቢያ .... 8-3

**Holy Trinity አርሜኒያዊ ቤተ-ክርስቲያን**፣ 145 Brattle Street፣ Sparks Street ላይ የሚገኘው የመኪና ማቆሚያ መግቢያ ..... 9-1

**Cambridge Water Department**፣ 250 Fresh Pond Parkway ............... 9-2

**Russel የወጣት ማዕከል**፣ 680 Huron Avenue፣ ሁለተኛ ፎቅ ... 9-3

**የPeabody ትምህርት ቤት ጂም**፣ 70 Rindge Avenue፣ የኋላ መግቢያ ........ 10-1

**የPeabody ትምህርት ቤት ጂም**፣ 70 Rindge Avenue፣ የኋላ መግቢያ ....... 10-1A

**Graham and Parks ትምህርት ቤት**፣ 44 Linnaean Street፣ የመጫወቻ ሜዳ መግቢያ ..... 10-2

**Cadbury Commons**፣ 66 Sherman Street፣ Cadbury Rd ላይ የሚገኘው የበረንዳ መግቢያ .................. 10-3

**Reservoir ቤተ-ክርስቲያን**፣ 170 Rindge Avenue፣ የኋላ መግቢያ ...... 11-1

**Reservoir ቤተ-ክርስቲያን**፣ 170 Rindge Avenue፣ የኋላ መግቢያ ... 11-1A

**Reservoir ቤተ-ክርስቲያን**፣ 170 Rindge Avenue፣ የኋላ መግቢያ ...... 11-2

**Burns አፓርታማዎች**፣ 50 Churchill Avenue፣ Community Room ..................... 11-3

**Burns አፓርታማዎች**፣ 50 Churchill Avenue፣ Community Room ................... 11-3A



# እ.ኤ.አ የ2025 ዓ.ም እጩዎች

## City Council (የከተማው ምክር ቤት)፡-

**Ayah A. Al-Zubi**፣ 156 Magazine Street
**Burhan Azeem**፣ 96 Berkshire Street *
**LaQueen Arleen Battle**፣ 86 Otis Street
**Elizabeth Bisio**፣ 22 Water Street
**Dana Ray Bullister**፣ 21 Brookline Street
**Timothy R. Flaherty**፣ 103 Fresh Pond Parkway
**John Hanratty**፣ 15 Mount Vernon Street
**Peter Hsu**፣ 70 Gore Street
**Marc C. McGovern**፣ 17 Pleasant Street *
**Ned S. Melanson**፣ 163 Allston Street
**Patricia M. Nolan**፣ 184 Huron Avenue *
**Stanislav A. Rivkin**፣ 17 Channing Street
**Zion Nathaniel Sherin**፣ 401 Washington Street
**Sumbul Siddiqui**፣ 283 Sidney Street *
**E. Denise Simmons**፣ 188 Harvard Street *
**Jivan G. Sobrinho-Wheeler**፣ 187 Brookline Street *
**Ayesha M. Wilson**፣ 305 Elm Street *
**Robert Winters**፣ 366 Broadway
**Catherine Zusy**፣ 202 Hamilton Street *

## School Committee (የትምህርት ቤት ኮሚቴ)፡-

**LaQueen Arleen Battle**፣ 86 Otis Street
**Alborz Bejnood**፣ 166 Auburn Street
**Alex Bowers**፣ 44 Pemberton Street
**Anne Mathilde Coburn**፣ 117 A Otis St
**Luisa de Paula Santos**፣ 51 Walker St
**Caitlin E. Dube**፣ 395 Huron Avenue
**Melanie Gause**፣ 269 Broadway
**Jessica Diaz Goetz**፣9 7 Pemberton St
**Richard N. Harding, Jr.**፣ 189 Windsor Street *
**Lilly Havstad**፣ 32 Granville Road
**Jane Hirschi**፣ 39 Rindge Avenue
**Elizabeth Hudson**፣ 325 Harvard Street *
**Caroline Mary Lisette Hunter**፣ 23 Rockwell Street *
**Arjun Kent Jaikumar**፣ 175 Richdale Avenue
**Jia-Jing Lee**፣ 20 2nd Street
**José Luis Rojas Villarreal**፣ 19 Cornelius Way *
**Eugenia Schraa Huh**፣ 259 Washington Street
**David J. Weinstein**፣ 45 S. Normandy Avenue *

* በድጋሚ ለመመረጥ የቀረቡ እጩ

## እጩዎቹን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ

ጋዜጦች፣ ድር-ጣቢያዎች እና በአካባቢው የሚገኙ ድርጅቶች እጩዎቹን ለሚመለከት መረጃ ጥሩ ምንጮች ናቸው። ብዙ እጩዎች ኦንላይን በመፈለግ ሊገኙ የሚችሉ የምርጫ ዘመቻ ድር-ጣቢያዎች አሏቸው።

በሕግ አስገዳጅ ከሚሆንበት ሁኔታዎች ውጪ የCambridge ከተማ አስተዳደር Election Commission የሚከተሉትን ጨምሮ ነገር ግን በእነዚህ ሳይገደብ ማናቸውም የምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴዎች ላይ አይሳተፍም፦

- የእጩዎቹ እምነቶች ወይም አቋሞች ዙሪያ መረጃ መስጠት
- የምርጫ ዘመቻ ቁሳቁሶች ላይ ቁጥጥር ማድረግ ወይም ሀቀኝነታቸውን ማረጋገጥ
- የእጩ ክርክሮችን ማዘጋጀት ወይም ማስተዋወቅ

### የምርጫ ዘመቻ ፋይናንስ፦

የCity Council እጩዎች የስቴት ጽሕፈት ቤት በሆነው Office of Campaign and Political Finance (የምርጫ ዘመቻ እና ፖለቲካዊ ፋይናንስ ጽሕፈት ቤት፣ OCPF) የምርጫ ዘመቻ ፋይናንስ ሪፖርቶችን ያስገባሉ።

የSchool Committee እጩዎች የምርጫ ዘመቻ ፋይናንስ ሪፖርቶችን ለElection Commission ያስገባሉ።

የምርጫ ዘመቻ ፋይናንስ ሪፖርቶችን ለማየት የሚከተለውን ይጎብኙ፦

**www.cambridgema.gov/cfr**

## ድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ ምን ይመስላሉ?

**ሶስት** ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ይኖራሉ፦ አንድ ለCity Council፣ አንድ ለSchool Committee እና አንድ ለድምጽ መስጫ ወረቀት ጥያቄው።

የድምጽ መስጫ ወረቀት ናሙናዎች የሚከተለው ላይ ኦንላይን ይለጠፋሉ፦

**www.cambridgema.gov/elections**

***የድምጽ መስጫ ወረቀት ጥያቄ መረጃ መራጭ ለሚገኝበት እያንዳንዱ መኖሪያ ቤት በፖስታ ተልኳል።***

# የPR ድምጽ መስጫ ወረቀትዎ ላይ ምልክት ማድረግ

ድምጽ መስጠት ቀላል ነው! የCity Council እና የSchool Committee ድምጽ መስጫ ወረቀቶች እጩዎችን ቁጥር ከተሰጣቸው ክቦች አጠገብ ይዘረዝራሉ። በቁጥር በተቀመጡት ክቦች ውስጥ ለእጩዎች በሚሰጡት የምርጫ ቅደም ተከተል መሰረት ለእጩዎቹ ደረጃ ይስጡ።

## ተቀባይነት ያላቸው ደረጃ አሰጣጦች

ቁጥር የተቀመጠበትን ክብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ በማድመቅ ምርጫዎችዎ ላይ ምልክት ያድርጉ።


መጀመሪያ ለሚመርጡት እጩ አንድ (1) ቁጥሩን ክብ ይሙሉ። ሁለተኛ ለሚመርጡት እጩ ሁለት (2) ቁጥሩን ክብ ይሙሉ፣ እንደዚህ እያደረጉ ይቀጥሉ።

ለሁሉም እጩዎች ደረጃ መስጠት አያስፈልግዎትም፦ አብዝተው ወይም አሳንሰው የፈለጉትን ያህል ምርጫዎች መሙላት ይችላሉ።


**ለአንድ እጩ አንድ ድምጽ ብቻ። በአንድ አምድ አንድ ድምጽ ብቻ።**

| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **Junior Mints፣** 95 Movie Road | | ① | ② | ③ | ● | ⑤ | ⑥ |
| **Three Musketeers፣** 333 Nougat Street | | ① | ● | ③ | ④ | ⑤ | ⑥ |
| **Werther Original፣** 753 Caramel Avenue | | ① | ② | ③ | ④ | ⑤ | ⑥ |
| **York Peppermint Pattie፣** 1940 Sensation Street | | ● | ② | ③ | ④ | ⑤ | ⑥ |
| **Marshmallow Peep፣** 432 Seasonal Lane | | ① | ② | ③ | ④ | ⑤ | ⑥ |
| **Good A. Plenty፣** 35 Licorice Street | በድጋሚ ለመመረጥ የቀረበ እጩ | ① | ② | ● | ④ | ⑤ | ⑥ |


## ተቀባይነት የሌላቸው ደረጃ አሰጣጦች



ለአንድ እጩ ከአንድ በላይ ምርጫ መሙላት



ተመሳሳይ ደረጃዎችን ከአንድ በላይ ለሆኑ እጩዎች መስጠት



ሙሉ በሙሉ ያልተሞሉ እና በማሽኑ ሊነበቡ የማይችሉ ክቦች

እያንዳንዱ ድምጽ መስጫ ወረቀት እጩዎችን በተለያየ ቅደም ተከተል አቀማመጥ ሊይዝ እንደሚችል ብቻ ያስተውሉ! የእጩዎቹ ስሞች በስማቸው የመጀመሪያ ሆሄያት ቅደም ተከተል በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ውስጥ ቦታቸውን ስለሚቀያየሩ፣ እያንዳንዱ እጩ እኩል ቁጥር ባላቸው ደምጽ መስጫ ወረቀቶች ላይ በሚፈለገው ራስጌ ሰፍረው ይታያሉ።

ስሕተት ከሠሩ ድምጽ መስጫ ወረቀትዎን ለምርጫ ሠራተኛው መመለስ እና ሌላ መውሰድ ይችላሉ። ድምጽ መስጫ ወረቀትዎን ለመሙላት የሚሰጡዎት ሦስት ሙከራዎች ብቻ ናቸው።

## ተመጣጣኝ ውክልና

እ.ኤ.አ ከ1941 ዓ.ም ጀምሮ የCambridge ከተማ አስተዳደር City Council እና School Committeeውን በተመጣጣኝ ውክልና (PR) ሲመርጥ ቆይቷል።

የዘጠኙ የCity Council አባላት እና የስድስቱ የSchool Committee አባላት ምርጫ እ.ኤ.አ በኖቬምበር ወር በጎደሎ ቁጥር ዓመታት ላይ ይካሄዳል።

PR ምርጫዎች ሁሉም ድምጽ ሰጪዎች በእኩልነት መወከላቸውን ያረጋግጣሉ። በተሰጡት ድምጾች አንድ አሥረኛውን የያዘ ማንኛውም የመራጮች ቡድን ከዘጠኙ የምክር ቤት አባላት ቢያንስ አንዱን መምረጥ መቻሉን የሚያረጋግጥ ቢሆንም፣ ብዙ መራጮች ያሉት ቡድን ግን አብላጫውን የምክር ቤቱን አባላት መምረጥ መቻሉን ማረጋገጥ ይችላል። አብላጫው በርካታውን ወንበር መምረጥ የሚችል ቢሆንም፣ አናሳዎቹ ቡድኖችም ግን ፍትሃዊ የውክልና ድርሻቸውን ያሸንፋሉ።

በተጨማሪም PR ምርጫዎች ድምጽ መስጫ ወረቀት አለመባከኑን ያረጋግጣሉ። ድምጽ መስጫ ወረቀትዎ የሚቆጠረው ለአንድ እጩ ብቻ ነው። እርስዎ በመጀመሪያ ደረጃ ላይ የመረጡት እጩ ከተሸነፈ ወይም ቀድሞውኑ ለማሸነፍ የሚበቃውን ድምጽ አግኝቶ ከሆነ ድምጽ መስጫ ወረቀትዎ ቀጣይ ለመረጡት እጩ ይተላለፋል።

ለአንድ እጩ ብቻ ደረጃ መስጠት ለዚያ እጩ የሚያስገኘው ለየት ያለ ጠቀሜታ ባለመኖሩ፣ ለፈለጉት የእጩዎች ብዛት ደረጃ ይስጡ።

# የPR ድምጽ መስጫ ወረቀቶች የሚቆጠሩበት መንገድ

## የመጀመሪያ ቆጠራ፦

ድምጽ መስጫ ወረቀቶቹ በእያንዳንዱ ድምጽ መስጫ ወረቀት ላይ በተሰጡት አንደኛ (#1) ድምጾች መሠረት ይለያሉ። እጩዎች በተሰጧቸው የአንደኛ ምርጫ ድምጽ ብዛት መሠረት በደረጃ ይቀመጣሉ።

## ኮታውን ማስላት፦

ኮታው የሚሰላው በሚከተለው ቀመር መሠረት ነው፦

$$\textbf{ኮታ=}\ \frac{\textit{ትክክለኛ የሆኑ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ብዛት}}{\textit{የሚመረጥ ቁጥር} + 1} + 1$$

ለምሳሌ፣ 24,990 ተቀባይነት ያላቸው ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ለCity Council ከተሰጡ ኮታው 2,500 ይሆናል (24,990 ሲካፈል በ10 ሲደመር 1)።

## ትርፉን ማሰራጨት፦

በአንደኛ (#1) ድምጾች አስፈላጊው ኮታ ላይ የደረሱ ማንኛውም እጩ ለሥልጣኑ መመረጣቸው ይታወጃል። ከኮታው ተጨማሪ ያገኟቸው ማናቸውም ድምጾች በድምጽ መስጫ ወረቀቱ ላይ ቀጣይ ለተመረጡት እጩዎች ይከፋፈላሉ። ለምሳሌ፦ ኮታው 2,500 ከሆነ እና እጩው 3,000 የመጀመሪያ ደረጃ ምርጫዎችን ካገኙ 500 ድምጾች ወደ ሌላ እጩ ይተላለፋሉ።

## እጩዎችን ማስወገድ፦

ቆጠራው ከሀምሳ በታች አንደኛ (#1) ድምጽ ያገኙ እጩዎችን በማስወገድ ይቀጥላል። የተሰጣቸው ድምጽ በተመረጠው ምርጫ መሠረት ቀጣይ ለተመረጡ ሌሎች እጩዎች ይሰራጫል። ከእያንዳንዱ ስርጭት በኋላ እያንዳንዱ እጩ ያገኙት ጠቅላላ የድምጽ ብዛት ይሠላል። ከዚያም ዝቅተኛ ድምጽ ያገኘ እጩ የተሸነፈ እንደሆነ ተገልጾ፣ የዚያ እጩ ድምጾችም ለመራጩ ቀጣይ የተመላከተ ምርጫ እንደገና ይሰራጫሉ።

## እጩዎችን መምረጥ፦

ጠቅላላ ድምጽ ላይ እንደገና የተሰራጩት ድምጾች ተደምረው በኮታው ላይ ሲደርሱ እጩው ለኃላፊነቱ መመረጣቸው የሚታወጅ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ ተጨማሪ ድምጽ አይተላለፍላቸውም። ይህ ሂደት ከዘጠኙ የCity Council አሸናፊዎች ወይም ከስድስቱ የSchool Committee አሸናፊዎች በስተቀር ሁሉም እጩዎች እሰከሚወገዱ ድረስ ይቀጥላል።

## የምርጫ ውጤቶች፦

በምርጫው ምሽት በቦታው ሳይገኙ ድምጽ የተሰጠባቸው ድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ጨምሮ በምርጫ ቀን በስካነሮች ያለፉ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች በሙሉ ይቆጠራሉ። በምርጫ ምሽት እያንዳንዱ ጣቢያ ለCentral Tabulation Center (ማዕከላዊ የድምጽ ቆጠራ ማዕከል) ሪፖርት ካደረገ በኋላ የመጀመሪያ ደረጃ ውጤቶች በ**www.cambridgema.gov** የCambridge ከተማ አስተዳደር መነሻ ገጽ ላይ ይለጠፋሉ።

ከምርጫው ቀጥሎ ካለው ቀን ጀምሮ ኮሚሽነሮቹ በጽሑፍ የገቡትን ሁሉንም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች እና ተጨማሪ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በእጅ ገምግመው ወደ ውጤቶቹ ይደምራሉ። ተጨማሪ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በስካነሮች መነበብ የማይችሉ ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ናቸው። እነዚህ ውጤቶች ሁሉም ድምጽ መስጫ ወረቀቶች ባለመካተታቸው ምክንያት አሁንም በይፋ ያልተረጋገጡ ውጤቶች ናቸው።

ከባህር ማዶ የተላኩ በጣቢያው ሳይገኙ ድምጽ የሚሰጥባቸው ድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ወይም ተቀባይነት ያላቸው ሆነው የተገኙ ተጠባባቂ ድምጽ መስጫ ወረቀቶችን ለመቁጠር ከምርጫው ከ10 ቀናት በኋላ የምርጫ ኮሚሽነሮች ይሰበሰባሉ። **እነዚህ የመጨረሻዎቹ ድምጾች ወደ ውጤቶቹ ከተካተቱ በኋላ ቆጠራው ይጠናቀቅ እና የElection Commission ሕጋዊ ውጤቶቹን ይፋ ያደርጋል።**

## በምርጫ ቀን የመሥራት ፍላጎት አለዎት?

Election Commission በምርጫ ቀኑ ላይ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ለመሥራት ፍላጎት ካላቸው የተመዘገቡ መራጮች የሚመጡ ማመልከቻዎችን ዓመቱን ሙሉ ይቀበላል።

ማመልከቻውን ከታች ከሚገኘው ድህረ-ገጽ ያውርዱ፦
**www.cambridgema.gov/ElectionWorkers**

በተጨማሪም ማመልከቻዎችን በElection Commission Office ማግኘት ይቻላል።

**የCambridge ከተማ አስተዳደር Election Commission**

689 Massachusetts Ave። STE 1፣ Cambridge፣ MA 02139-3302 • **ስልክ፡-** 617-349-4361
**ፋክስ፡-** 617-349-4366 • **ኢሜይል፡-** elections@cambridgema.gov

በቅድሚያ የተሰናዳ STD
የUS ፖስታ አገልግሎት
የተከፈለበት
CAMBRIDGE MA
የፈቃድ ቁጥር 58215

**ኮሚሽነሮች፡-**
Ethridge A. King, Jr.
Larry W. Ward
Charles J. Marquardt
Thomas J. Stohlman Jr.

**ሥራ አስፈጻሚ ዳይሬክተር፡-**
Tanya L. Ford

**ረዳት ዳይሬክተር፡-**
Lesley A. Waxman

ነዋሪ ደንበኛ
Cambridge, MA

# እ.ኤ.አ ኖቬምበር 4 ቀን 2025 ዓ.ም ለሚውለው የማዘጋጃ ቤት ምርጫ 24-ሰዓት የሚያገለግሉ ይፋዊ የElection Commission ድምጽ መስጫ ሳጥን መገኛዎች።

## ዋና የድምጽ መስጫ ሳጥን መገኛ

የሚከተሉት ቦታዎች እ.ኤ.አ ከሰኞ፣ ኦክቶበር 6 ቀን 2025 ዓ.ም ጀምሮ የምርጫ ቀን እስከሚውልበት እ.ኤ.አ ማክሰኞ፣ ኖቬምበር 4 ቀን 2025 ዓ.ም 8 ፒ.ኤም ድረስ ክፍት ይሆናሉ።

**689 Massachusetts Ave**
በፊት ለፊት መግቢያው የግራ ጎን

**እ.ኤ.አ ኖቬምበር 4 ቀን 2025 ዓ.ም ላይ በሚውለው የምርጫ ቀን ክፍት የሚሆነው የድምጽ መስጫ ሳጥን መገኛ ይህ ብቻ ነው።**

## ድምጽ መስጫ ሳጥን የሚገኝባቸው ሌሎች ቦታዎች

የሚከተሉት ቦታዎች እ.ኤ.አ ከሰኞ፣ ኦክቶበር 6 ቀን 2025 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኞ፣ ኖቬምበር 3 ቀን 2025 ዓ.ም 8 ፒ.ኤም ድረስ ክፍት ይሆናሉ። **ድምጽ መስጫ ሳጥን የሚገኝባቸው ሌሎች ቦታዎች የምርጫ ቀን በሚውልበት እ.ኤ.አ ኖቬምበር 4፣ 2025 ዓ.ም ላይ ክፍት አይሆኑም።**

**City Hall**
795 Massachusetts Avenue
ከኋለኛው መግቢያ በር አቅራቢያ

**Morse ትምህርት ቤት**
40 Granite Street
ከፊት ለፊት መግቢያ በሩ አቅራቢያ

**Cambridge Police Headquarters (የCambridge ፖሊስ ዋና መሥሪያ ቤት)**
125 6th Street
ከህንፃው ፊት ለፊት አቅራቢያ

**Maria L. Baldwin ትምህርት ቤት**
85 Oxford Street
በOxford St. መግቢያ በቀኝ ጎን በኩል

**O'Neill ቤት-መጻሕፍት**
70 Rindge Avenue
ከመግቢያው ደረጃዎች አጠገብ

! እባክዎ **የመረጡበት ድምጽ መስጫ ወረቀት የጁራት ፖስታው** (ቢጫ ፖስታ) ውስጥ የታሸገ መሆኑን እና ፖስታውን ድምጽ መስጫ ሳጥን ውስጥ ከማስገባትዎ በፊት የጁራት ፖስታው ላይ ያለው ማረጋገጫ **የተፈረመበት** መሆኑን ያረጋግጡ።

## ባለብዙ ቋንቋ አጋዥ ግብዓቶች

বাংলা
አማርኛ
عربى
Español
中文
Português
Kreyòl
English